ቅሬታዋ ቤተ ክርስቲያን እና

የኋለኛው ዝናብ

በሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን



ዘንዶውም በሴቲቱ ላይ ተቈጥቶ የእግዚአብሔርን
ትእዛዛት የሚጠብቁትን የኢየሱስም ምስክር ያላቸውን
ከዘርዋ የቀሩትን ሊዋጋ ሄደ፤ ራዕ 12፡18

መግቢያ

ይህንን ጹሑፍ በአብዛኛው ከትንቢት መንፈስ ተውጣጥቶ የተዘጋጀ ነው በጸሎት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በማገናኘት እንድታጠኑት በጌታ ፍቅር አሳስባለሁ ጌታ የጠራን ምስክሮቹ እንድንሆን አና ኃጥያትን እንድንጠላ ነው። ማናችሁም በምንም አይነት ኃጥያት ውስጥ ብትሆኑም የክርስቶስ ፍቅር ሁሌም ይታወሳችሁ። በንስሃ ወደ ጌታ ለመቅረብ ልባችሁ ይናፍቅ፤ የህይወት ጠላት የሆነውን የዲያቢሎስን ክስ አትስሙ፤ የክርስቶስ ደም የማያነጻው ኃጥያት የለም፤ እርሱ ወዳለበት ወደ ቅድስተ ቅዱሳን በእምነት እንቅረብ

ጌታ ይባርካችሁ

መልካም ንባብ

አዘጋጅ ጌታያውቃል ዮሐንስ

ሰኔ 2012 ዓ.ም/ 2020 G.C

የእግዚአብሔር ቅሬታዋ ቤተክርስቲያን እና ተልዕኮ

የቅሬታን ትክክለኛ ትርጉም ለማብራራት መጀመር ያለብን ከሐዋርያት ቤተ ክ/ያን ነው በሐሰተኛ ትምህርት ያልተበከለችው የሐዋርያት የመጀመርያዋ ቤተ ክ/ያን ትምህርት እና አካሔድ እንዲሁም እምነት ጋር ተመሳሳይ ውሳኔና ባህሪይ በዛሬው ቤተ ክ/ያን ውስጥ በማየት በማመዛዘን ነው። -ሐዋ 2፡42-47

ቤተ ክ/ያኗ በመንፈስ የምትመራ ከእግ/ር የተቀበሉትን መልዕክት ለዓለም የሚያዳርሱ በአንድነት እና በህብረት የሚጸልዩ (የሐዋ 2፡42-47) ሰንበትን የሚጠብቁ፤ (የሐዋ 16፡13) ታማኞች፤ ያላቸውን ሁሉ በጋራ የሚጠቀሙ፤ በየሥጦታቸው ሁሉ ነፍስትን ለማዳን ሌተ ቀን የሚተጉና በታላቁ የሥደት የሞት ና የመከራ ግዜ ውስጥ አልፈው ለክብሩ የሚቆሙ የእግ/ር ምስክሮች ናቸው።

<u>ቅሬታ ማለት ምን ማለት ነው?</u>

“ቅሬታ” የሚለው ቃል በብሉይ ኪዳን ሆነ በአዲስ ኪዳን <u>በ 3</u> ምክንያቶች የተሰየመ ስም ነው።

ቅሬታ በብሉይ ኪዳን

<u>1. ታሪካዊ ቅሬታዎች</u> ከቃሉ እንደምንረዳው የእግ/ር ምህረት በዝቶላቸው ከምርኮ ሀገር፤ (ነህ 1፡1-2) ፤ከጦርነት (ዕዝ 9፡13-14) እና ከረሃብ (45፡7) እነዚህ የተረፉ የእግ/ር ቅሬታ/ ህዝቦች ወይም ትሩፋን መሆናቸው ነው።

“ እግዚአብሔር በምድር ላይ ቅሬታን አስቀርላችሁ ዘንድ ከእናንተ በፊት ላከኝ።” ዘፍ 45፡7

“... አምላካችን ስለ ኃጥያታችን ብዛት አልቀሰፍከንም ነገርግን ቅሬታን ሠጠኸን።” ዕዝ 9፡13

2. <u>ታማኝ ቅሬታዎች</u> ፍጹም ሳይነቃነቁ በጸጋው የቆሙና የተመረጡ ቅዱሳን ለእግ/ር ህግ የሚታዘዙ ና በትዕግስታቸው የሚጸኑ የእግ/ር ቅዱሳን ናቸው ያመለክታል። ይህም ሀጥያት የጠሉ(ዘፍ 6፡8) ለበዓል ያልሰገዱ(1 ነገስ 19፡ 14 ና 18) እንዲሁ ቅዱሳን ሆነው የተመረጡ (የተቀበሉ) (ኢሳ 4፡2-4)

“እኔም ከእስራኤል ጉልበታቸውን ያላንበረከኩትን ሁሉ በአፋቸውም ያልሳሙትም ሁሉ ሰባት ሺ ሰዎች ለእኔ አስቀራለሁ።” 1ነገስ 19፡18

3. <u>ከፍርድ የዳኑት ቅሬታዎች</u> ሁሉንም የዓለም ፈተና ተቋቁመው በማለፍ ፍጹምነታቸው የተመሰከረላቸው እና የተፈረደላቸው እንዲሁም ያባታቸውን መንግስት ዕርስት የሚወርሱ ማለት ነው። ዘካ 13፡8-9 ኢሣ 66፡19-20

“ በመካከላቸውም ምልክት አደርጋለሁ ከእነርሱ የዳኑትን ዝናዬ ወዳልሰሙ ክብሬንም ወዳላዩ... በሩቅም ወዳሉ ደሴቶች እልካቸዋለሁ በአሕዛብ መካከል ክብሬን ይናገራሉ።” ኢሣ 66፡19

<u>ቅሬታ በአዲስ ኪዳን</u>

የደህንነት እቅድ ተልዕኮ ለዓለም የሚዳረሰው በቅሬታው ህዝብ ብቻ ነው። (ማቴ 20) “ እስራኤል የሆኑ ሁሉ አይድኑምና”።(ሮሜ 9፡27... 11፡5)

እሥራኤል የሆነ ሁሉ የእግ/ር መንግስት አባል አይደለምና፤ ወደ የሱስም መጥተው በመስማት ከህዝቡ የሚቀላቀልም ሁሉ እውነተኛ የእርሱ ተከታይ አይደለም።

ይሁን እንጂ ከመጽሐፍ ቅዱስ ከስደት ብቻ መትረፍ እንደ ሙሉ መስፈርት አያስቀምጠውም። ምክንያቱም የእግ/ር ትሩፋን ሲሰደዱት የተሸከሙት የእግ/ር እውነት ያላቸው ነውና። ይህም የታማኝነታቸውን መለኪያ የሆነው የእግ/ር ህግ የየሱስ ምስክር(የትንቢት መንፈስ) ያላቸው ራዕ 19፡10 እና የየሱስ ሃይማኖት አላቸው። ራዕ 12፡17 እና 14፡12 በአዲስ ኪዳን የነበሩት ቅዱሳን ያደረጉት ይህን ነበር።

“የየሱስ ሀይማኖት” ማለት ምን ማለት ነው?

ዓ/ም	የተገለጠው የእውነት ብርሃን	የዘመኑ ቅሬታዎች
	የመጽሐፍ ቅዱስ ስልጠና	ዋይክሊፍ
1370	ለእግ/ር መታዘዝ	ሐስ
1517	ደህንነት በጸጋ	ሉተር
1555	የህሊና ነጻነት	ካልቭን
1650	የጥልቀት ጥምቀት	ዊሊያም
1705	የክርስቶስ መለኮት	ዊስሌይ
1844	የዳግም ምጻት ተስፋ	ሚለር

“የእግ/ር ቅሬታ ህዝቦች በአለም ፊት አዳሾች ሆነው ይቆማሉ። ይህም ሲሆን 4 ትዕዛዝ የሆነው የ7 ቀን ሰንበት የፍጥረት ማስታወሻ መሆኑ ይመሰክራሉ። coflict and courage p269. ዘፍ 2:4

የ7ኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተ ክ/ያን ባቢሎን ነች?

በአሁኑ ሁኔታ የ7 ቀን አድቬንቲስት ባቢሎን ናትየሚሉ ሰዎች በብዛት መጥተዋል። በርግጥ ራዕ 18፡2 ስለ ባቢሎን የርኩሰት ሁሉ ምንጭ መሆኗ ቢናገርም ይህች የኛ ቤተክርስትያን አካል ነች ማለት አይደለም። እኛስ ከሃዲ እስራኤላዊያን ነን? በርግጥ አዎ። በቤታችን ውስጥ እጅግ የሚበዙ አገልጋዮች የእግ/ር እውነት ክህደት ውስጥ የገቡ ቢሆንም በጣም ታማኝ እውነተኛ የእግ/ር አገልጋዮችም አሉ።

የትንቢት ጹሁፍ ማብራሪያ

1.7ኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተ ክ/ያን ባቢሎን ናት የሚሉ ሰዎች እቤታቸው ቢቀሩ ይሻል ነበር። TMM p37

2.7ኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተ ክ/ያን ባቢሎን ናት ብሎ መስበክ የወንድሞች ሁሉ ከሳሽ ከሆነው ሰይጣን ከሰበከው ስብከት ጋር አንድ ነው። TMM p42

3.7ኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተ ክ/ያን ባቢሎን ናት በሚሉ ሰዎች የተጠነሰሰው እግ/ር በአለም ላይ ቤተ ክርስቲያን እንደሌለው የሚወድ ነው። TMM p45

4.‹‹ስለ ታላቁ ጩኸት ትራክት(ፅሁፎችን) ያሰራጩት ሰዎች በጉዳዩ አላማከሩኝም እነርሱ ከነ ፅሁፎች በመጥቅስ የራሳቸውን አስተያየት ጨምረውበታል እነዚህ ሰዎች 7ኛ ቀን አድቬንቲስት ባይብልን እንደሆነች እንደወደቀችና ሰዎችም ለመዳን ከርሷዋ በመውጣት እንዳለባቸው ከእግዚአብሔር ዘንድ መልዕክት ተሰጥቶናል ይላሉ Review and Herald Novemeber 8 1856

5.ዛሬም 7ኛ ቀን አድቬንቲስት ባቢሎን ነች የሚለውን ተመሳሳይ ስብከት እንሰማለን ይህ ሊሆን አይችልም አንድ ሰው 7ኛ ቀን አድቬንቲስት ባቢሎን እንደሆነች ይሰብክ ነበር ግን እርሱ ስህተት ውስጥ እንደገባና እውነት ምን እንደሆነ ለይቼ ገለፅኩለት Manuscript relases coll 298

6.አይደለም 7ኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን ባቢሎን ፈፅሞ ለወደፊትም ባቢሎን ልትሆን እንደማትችል እግዚአብሔር ግልፅ ማስረጃ አሁንም እላለሁ የእግዚአብሔር ትዕዛዛት የምትጠብቅ ቤተክርስቲያን ባቢሎን እንደሆነች ለሚናገር ሰው የእግዚአብሔር ምንም ምልክት አልሰጠም Selected message book 2 p 68

7.ዛሬም ቢሆን የእ/ር ቤተክርስቲያንን መናፍስትና የወፎች መጠለያ እንድትሆን ለማድረግ ከሚያደቡት መካከል ጥቂቶች፡-

8.“ የጥንት አይሁዳዊያን ከጣኦት አምልኮ መንግስታት ጋር ቤተሰባዊ ግንኙነት ፈጥረው ከእግ/ር እንደራቁ ሁሉ የየሱስ ቤተ ክርስቲያንም እግ/ር ከማያምኑ ጋር በተሳሳተ መልክ አየተገናኙ በአሁኑ ወቅት የእውነት ህይወቷን የሚመራ መለኮታዊ ብልሀት እየተወች ነው። ታላቁ ተጋድሎ. 335

“ከእርሷ ውጡ”

‹‹ ከዚህ በኋላ ታላቅ ስልጣን ያለው ሌላ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ፥ ከክብሩም የተነሣ ምድር በራች። በብርቱም ድምፅ። ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች፥ ወደቀች፥ የአጋንንትም ማደሪያ ሆነች፥ የርኵሳንም መናፍስት ሁሉ መጠጊያ የርኵሳንና የተጠሉም ወፎች ሁሉ መጠጊያ ሆነች፤›› ራዕይ 18፡1-2

ከዚህ ምዕራፍ ላይ የተጠቀሰው መልአክ በራዕይ 14 የተናገረው ሁለተኛው መልአክ በሀይል ሲደገም ከክርስቶስ ዳግም መምጣት በፊት ምን እንደሚሆን የሚያሳይ ነው።።

<u>ታድያ እነዚህ እርኩሳን መናፍስትና የተጠሉ ወፎች በከሃዲዋ ቤ/ክ ውስጥ መጠጊያ ያገኙ ምንን ያመለክታሉ?</u>

በመጀመርያ እነዚህ ርኩስ መናፍስት በሮም ቤ/ክ የተጀመሩ ግን በተከታዮቹ አብያተ ክ/ናት ደግሞ ተቀባይት ያገኙትን የሀሰት አምልኮ ተግባራት ይወክላሉ። ከእነዚህም ጥቂቶቹ ለምሳሌ <u>የድንግልና ቅድስና ቅዱሳን አምልኮ፤ የስእል አምልኮ፤ ሀሰተኛው ሰንበት (እሁድ አምልኮ)፤ የክህነት ውርስ፤ በጥምቀት መዳን፤ ፒርግቶሪ፤ ቅጣት፤ ኑዛዜ፤ ለሙታን መጸለይ፤ እንዲሁ ሌሎች ና ሀሰተኛ ትምህርቶች ይገኙበታል። ዘመናዊነትም ከርኩሳን መናፍት አንዱ ሲሆን ጳውሎስ በዘመናችን የሚኖር ቢሆን ኖሮ ‹‹ ሌላ ወንጌል›› ብሎ እንደሚጠራው ጥርጥር የለውም። ገላ1፡9 የዘመናዊነት አምልኮ እግ/ር ፈጣሪ የፍቅር አምላክና የቃሉ ባለቤት መሆኑ አይቀበልም። ለክርስቶስ ሰባዊነትም ቦታ የለውም።</u>

<u>የመናፍስት አምልኮ(spiritualism) ከዲያቢሎስ ትምህርቶች አንዱ ሲሆን መጀመርያ እባብ በተናገረው የሀሰት ት/ት ጋር የተያያዘ ነው። የሙታን ህያዋንነት ነው። የክርስት ና እምነት ግን ለእነዚህ አይነት የሀሰት ት/ት ቦታ አይሰጠውም። በእነዚህ ዘመናዊ እርኩሰት መናፍስት ና የመናፍስት አምልኮ በመጠቀም ሰይጣን ብዙ ፕሮቴስታንትን አብያተ ክ/ናት እያደከመ የካቶሊክ እንቅስቃሴ(Catholicing movement) ወደ ኃላ መለስ በለው ያችን ዓመንዝራ እናታቸውን (ባቢሎንን) እንዲከተሉ አድርጎቸዋል።</u>

በዚህ የተነሳ ከሃዲ ፕሮቴስታንቶች የሰይጣን የእርኩሳን መናፍስት የተጣሉ ወፎች መጠጊያ ቢሆንም የሚገርመው ነገር አይደለም ። የባቢሎን የመጀመርያ ችግር እውነትን ከሀሰት መቀላቀል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የክርስቶስን ሰባዊነት መካድ ነው። ሀገ ወጥ ጥምረት ሲሆን የቤ/ክ የመንግስት መጎዳኘት፤ የፖለቲካ አባልነት ማስፋፋት መተግበር እንዲሁ ምእመንን ለመቆጣጠር ፖለቲካ ስልጣንን መጠቀም የመሳሰሉት ናቸው።

ታድያ የባቢሎን ፍርድ በተቃረበበት ክርስቶስም ሊመጣ ባለበት ወቅት ከመቅሰፍቶቹ ለማምለጥ የእግ/ር ሰዎች በሶስቱ መላዕክ መልክት ለቀው የሚወጡበት በዚህ ወሳኝ ሰዓት ላይ ነው ቆመናል? 1ተሰ1፡9-10

‹‹ በራዕይ 14 የተነገረው ባቢሎን መውደቅ ባንድ ወቅት ንጹሐን የነበሩ በኃላ ግን የወደቁት ከሀዲ ፕሮቴስታንቶች ኃይማኖታዊ ጭምር ማመልከቱ እንጂ የሮም ቤ/ክ ብቻ የጠቀስ ሊሆን አይችልም ።›› ታላቁ ተጋድሎ 331

<u>የሎዶቅያ እንቅስቃሴ</u>

‹‹በሎዶቅያም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ። አሜን የሆነው፥ የታመነውና እውነተኛው ምስክር፥ በእግዚአብሔርም ፍጥረት መጀመሪያ የነበረው እንዲህ ይላል።›› ራእይ 3፡14

በኤሺያ ለሚገኙ 7ቱ አብያተ ክርስቲያን በዘመናት ውስጥ የነበሩት አብያተ ክርስትያናት ይወክላሉ።

ታድያ በመጨረሻ ዘመን ላይ ያላቸውን ቤ/ክ እንደመሆኑ መጠን ‹‹ላውዶቅያ›› የሚለው የቃል ትርጉም “በፍርድ ዘመን ውስጥ የሚገኝ ህዝብ” ማለት ነው።

ላውዶቅያ ኤሽያ ውስጥ ከሚገኙ ከተሞች አንዱ የነበረችና ካላት ልዩ ታሪክ ግን የመጨረሻ ዘመን ቤተ ክርስቲያን የምትወክል ትንሽ ከተማ ነበረች ።።ላውዶቂያ የሚባለው ስም ለውዳሴ ለምትባለው የኦርቶዶክስ 2ኛውን ንጉስ ከክ.ል በ ከ 216-246 ዓ.ዓ የተሰየመ ሲሆን ቀስ በቀስ በሀብትም ሆነ በኢኮኖሚ እያደገች መጣች።።ቢሆንም ላውዶቂያ ከተማ ግን በ60 ዓ.ም በመሬት መንቀጥቀጥ ምክንያት ከጎረቤታቿ ምንም እርዳታ ጠይቃ አታውቅም።።ይህ ደግሞ ‹‹ያለኝ ይበቃኛል ከሌላ ምንም ነገር አልሻም››ማለቷን ያመለክታል።።

በዚህ መሰረት በመጨረሻ ዘመን ውስጥ ለምትገኝ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ልትሆን ችላለች።።ታዲያ በዚህ ላውዶቂያ እንቅስቃሴ ከ1844ቱ ዓ.ም ክርስቶስ ሊቀካህናችን ወደ ሰማያዊ መቅደስ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን በመግባት የፍርድ ምርመራ (የሙታን) ከመጀመሩ ጋር የተያያዘ ነው።።ይሁን እንጂ በመጨረሻው ዘመን ላይ የተነሳችው ይህች ቅሬታዋ ቤ/ክ (7ተኛ ቀን አድቬንቲስት) ሙሉ በሙሉ የተሰጣትን ተልዕኮ እንድትፈፅም የተሰጣትን እውነት ተቀብላ በለብታ ህይወቷ በግዜው ልትወጣ ባለመቻሏ ትነቅፋለች መነቀፍም ብቻ ሳይሆን ከዚህ ከለብታ ሁኔታዋ በመመለስ ንስሃ ካልገባች እንደምትጠፋም ተነግሯታል።።

- በ1888 አ.ም የላውዶቂያ እንቅስቃሴ ወደ ፍጻሜ አምጥቶ ህዝቡን ወደ ሰማያዊ ከነአን ለማስገባት እግዚአብሔር እስከ ዛሬ ይህንን እንቅስቃሴ እየመራና በፍቅር እየተንከባከው ነው
- ዘዳ 7፡6-9 ለአምላክህ ለእግዚአብሔር አንተ ቅዱስ ሕዝብ ነህና በምድር ፊት ከሚኖሩ አሕዛብ ሁሉ ይልቅ ለእርሱ ለራሱ ሕዝብ ትሆንለት ዘንድ አምላክህ እግዚአብሔር መረጠህ። እግዚአብሔርም የወደዳችሁና የመረጣችሁ ከአሕዛብ ሁሉ በቍጥር ስለ በዛችሁ አይደለም እናንተ ከአሕዛብ ሁሉ በቍጥር ጥቂቶች ነበራችሁና....

ነገር ግን እግዚአብሔር ስለ ወደዳችሁ ለአባቶቻችሁም የማለላችውን መሐላ ስለ ጠበቀ፥ ስለዚህ እግዚአብሔር በጽኑ እጅ አወጣችሁ፥ ከባርነትም ቤት ከግብፅ ንጉሥ ከፈርዖን እጅ አዳናችሁ። አንተም አምላክህ እግዚአብሔር እርሱ አምላክ እንደ ሆነ፥ ለሚወድዱትም ትእዛዙንም ለሚጠብቁ ቃል ኪዳኑንና ምሕረቱን እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ የሚጠብቅ የታመነ አምላክ እንደ ሆነ እወቅ

የጥንታዊ እስራኤላዊያን ካለመታዘዛቸውና ከእምቢተኝነታቸው ተምልሰው ንስሀ የማይገቡ ከሆነ እንደምወገዱ (እንደምጠፉ) ተናግሯቸው

ራዕይ 3፡20-22 የመጨረሻ ዘመን ቤተክርስቲያንም በተመሳሳይ አደጋ ላይ ነው ያለችው ስለዚህ የላውዶቂያ ቤተክርስቲያን ብቸኛው ተስፋ እውነትን ፤በረከትና የክርስቶስን ፀጋ መሸለም ብቻ ነው ራዕይ 19፡8

መተፋት ምንድን ነው?

መተፋት በእስራኤላዊያን ዘመን ሊቀካህናቸው በአመት አንድ ጊዜ ወደ ቅድስተ-ቅዱሳን ገብቶ የስርየት አገልግሎት ሊያከናውን ከሚፈልግባቸው ተግባራት ከማከናወን ስታቀቡ የሚደርስባቸው ነገር ሲሆን ትርጉሙ ‹‹መቆረጥ መገንጠል ወይም ከእግዚአብሔር መለየትን›› የሚያመለክት ነው በላውዶቂያ ህይወት ይህ ተመሳሳይ ድርጊት ሊደርስ የሚችለው የተሰጣትን ጊዜና ሀላፊነት በተገቢው መንገድ ሳትጠቀም ከቀረች ብቻ ነው

የላውዶቂያ ዘመን በሁለት ይከፍላል

1.የሙታን ፍርድ ምርመራ የዮሐንስ ራዕይ 20፡11 ታላቅና ነጭ ዙፋንን በእርሱም ላይ የተቀመጠውን አየሁ፥ ምድርና ሰማይም ከፊቱ ሸሹ ስፍራም አልተገኘላቸውም። ሙታንንም ታናናሾችንና ታላላቆችን በዙፋኑ ፊት ቆመው አየሁ፥ መጻሕፍትም ተከፈቱ...

ሌላ መጽሐፍም ተከፈተ እርሱም የሕይወት መጽሐፍ ነው፤ ሙታንም በመጻሕፍት ተጽፎ እንደ ነበረ እንደ ሥራቸው መጠን ተከፈሉ።

2.የህያዊያን ፍርድ ምርመራ

1 ጴጥ 4፡17 ፍርድ ከእግዚአብሔር ቤትተነሥቶ የሚጀመርበት ጊዜ ደርሶአልና፤ አስቀድሞም በእኛ የሚጀመር ከሆነ ለእግዚአብሔር ወንጌል የማይታዘዙ መጨረሻቸው ምን ይሆን? ታዲያ መተፋት ማለት በህይወት እያሉ የሰው ስም ከህይወት መዝገብ ወይም የሰሩት መልካም ስራ መፋቅ ነውና የህያዋን ፍርድ እስካልተጀመረ ድረስ እከሌ ተተፍቷል ማለት ይከብዳል ለመሆኑ የሊቀ ካህን ወደ ቅድስተ-ቅዱሳን መግባት ጋር በተያያዘ ከህዝብ የሚፈልጉት ተግባራት ምንድናቸው?

ዘሌዋ 23፡27 በዚህ በሰባተኛው ወር አሥረኛው ን የማስተስረያ ቀን ነው የተቀደሰ ጉባኤ ይሁንላችሁ ሰውነታችሁን አስጨንቁት፥ ለእግዚአብሔርም የእሳት ቍርባንን አቅርቡ። በአምላካችሁም በእግዚአብሔር ፊት ማስተስረያ ይሆንላችሁ ዘንድ የማስተስረያ ቀን ነውና በዚያ ቀን ሥራ ሁሉ አትሥሩ። በዚያም ቀን የማይዋረድ ሰው ሁሉ ከሕዝቡ ተለይቶ ይጥፋ።

ዘሌዋ 23፡23 እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው።

ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው። በሰባተኛው ወር በመጀመሪያው ቀን ዕረፍት፥ በመለከት ድምፅ መታሰቢያ፥ የተቀደሰ ጉባኤ ይሁንላችሁ።

ስለዚህ ሊቀ ካህኑ ወደ ቅ/ቅዱሳን ከመግባቱ አስቀድሞ መለከት የሚነፋ ሲሆን ህዝቡን ካህኑ ወዳለበት ስፍራ ለማሰባሰብ የሚቀጥል ስራ ነው ህዝቡ ለነፍሳቸው ደህንነት ሲሉ ልባቸውን በመመርመር በቤተመቅደሱ ወደ ቅደስተ ቅዱሳን ገብቶ ሳለ በቤቱ በመገኘት ከህዝቡ ተለይቶ ስራውን እንዲያከናውን አይጠበቅበትም...

ገፅ 11

ይልቅ ራሱን አዋርዶና ልቡን ፈትሾ ንስሃ በመግባት በመቅደሱ ዙሪያ በመገኘት እንድጸልይ ይገደዳል ማለት ነው ይህንን ሳያደርግ ቢቀር ግን ከህዝቡ ይቆረጣል ።።

እግዚአብሔር ቀድሞ እስራኤልን ጠላቸው? በፍጹም

ለራባቸውም ከሰማይ እንጀራ ሰጠሃቸው፥ ለጥማታቸውም ከዓለቱ ውኃ አመጣህላቸው ወደ ማልህላቸውም ምድር ገብተው ይወርሱ ዘንድ አዘዝሃቸው። ነገር ግን እነርሱና አባቶቻችን ታበዩ፥ አንገታቸውንም አደንደኑ፥ ትእዛዝህንም አልሰሙም፥ ለመስማትም እንቢ አሉ፥ ያደረግህላቸውንም ተአምራት አላሰቡም አንገታቸውንም አደንደኑ፥ በዓመፃቸውም ወደ ባርነታቸው ይመለሱ ዘንድ አለቃ አደረጉ አንተ ግን ይቅር ባይ፥ ቸርና መሐሪ አምላክ፥ ለቍጣም የምትዘገይ፥ ምሕረትንም የምታበዛ ነህ፥ አልተውሃቸውም።

ለቅሬታዋ የክርስቶስ መልዕክት

የላውዶቅያ ታላቅ ፍላጎት

በክርስቶስ እና በሰይጣን መካከል ያለው ታላቁ ተጋድሎ(ክርክር) ወደ መደምደሚያ እየተቃረበ ነው።። ሰይጣን በመጨረሻው በዚህ ጊዜ በሰብአዊ ታሪክ ከሰራው ስራ ይበልጥ ለመስራት ሂደቱን አጠናቁል።።

በራዕይ 12፡12‹‹...ለምድርና ለባሕር ወዮላቸው÷ ዲያብሎስ ጥቂት ዘመን እንዳለው አውቆ በታላቅ ቍጣ ወደ እናንተ ወርዶአልና።›› ተብሎ ተነግሮናል።።

በ1ጴጥ 5፡8 ‹‹በመጠን ኑሩ ንቁም÷ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና፤›› ይህን የመሰለ ማስጠንቀቂያ ለቅሬታዋ ቤተ-ክርስቲያን አምላክ ተሰጥቱታል።።

‹‹አስጊ ጊዜያት በፊታችን ናቸው። እውነትን የሚያውቅ ሁሉ መንቃትና ራሱን፣ አካሉና መንፈሱን በአምላክ አሰልጣኝነት ሥር ማኖር አለበት። ጠላት በድንካኖችን ላይ ነው።ከእርሱ ለመጠበቅ በጣም ንቁዎች መቦን አለብን።የአምላክን ሙሉ ዕቃ ጦር መልበስ አለብን። በትንቢት መንፈስ አማካኝነት የተሰጡንን ምክሮች መከተል አለብን።ለዚህም ጊዜ የሆነውን እውነት ማፍቀር እና መታዘዝ አለብን። ይህም ብርቱ ማታለያዎችን ከመቀበል ያድነናል።‹‹... እግዚአብሔር ለቤተክስቲያን በተሰጡ ምክሮች ያሁኑን ተግባራችንና አሁን ልንይዝ ያለብንን አቋም ይገልጽ ዘንድ በረዱን መጽሐፎች አማካይነት ነግሮናል። መስመር በመስመር ትዕዛዝ በትዕዛዝ ላይ የተሰጡንን ማስጠንቀቂያዎች መቀበል አለብን። ችላ ብንላቸው ምንም ምክንያት (ማመኻኛ) ልናቀርብ እንችላለን?” 8T298

መጋቢው ጳውሎስ ስለ ምናደርግው ውጊያ እንዲህ በማለት ይመክረናል፤

‹‹ በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ።የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ።መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና÷ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፉት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።ስለዚህ በክፉው ቀን ለመቃወም÷ ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሡ።እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ÷ የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ÷ በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙበሁሉም ላይ ጨምራችሁ የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነትን ጋሻ አንሡ፤የመዳንንም ራስ ቁር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ፤ በዚህም አሳብ ስለ ቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በመጽናት ሁሉ ትጉ፤›› ኤፌ 6፡10-18

ኃጥያትን ለማሸነፍ ያለው ብቸኛው አማራጭ በክርስቶስ መሆን ነው። ይህም በክርስቶስ ስንሆን መጋቢው ጳውሎስ ሲያብራራው አንድ ወታደር ለውጊያ ሲወጣ ለውጊያ በሚያስ ፈልገው እቃዎች ይመስለዋል። እውነት ነው ኃጥያትን በራሳችን ለመተው የምንታገው ትግል ዋጋ የለውም፤ ትግሉ ላይ ማሸነፍ የምንችለው በክርስቶስና በክርስቶስ ብቻ ስንሆን ነው።

የምንዘጋጅበት ጊዜ።

በዚህ በጨለማው የምድር ታሪክ ሰዓት ከአምላክ ዙፋን የሚያበራ የብርሃን ጮራ ሁሉ በርግጥ የሚያስፈልገን ነው። ዓለምን ታላቅ መከራ የሚቆየው መሆኑን እናውቃለን ነገር ግን ፤5T፰፩፲፩ ውስጥ ‹‹ የእግዚአብሔር ሕዝብ ታላቅ መከራ ይቆያቸዋል›› የሚል እናነባለን።

ክርስቶስ በምድር ሲኖር የተንደላቀቀ ኑሮ አልኖረም። እንዲሁም ለእርሱ ተከታዮችና እርሱን ለመምሰል ለሚጥሩ ሁሉ ከአለም ጥሩ ነገር እንዳይጠብቁ ነግሩቸዋል። ቤተ ክርስቲያንም በዚሁ መከራ እንደምታልፍና አሸንፋ እንደምትቆም ቅዱስ መጽሐፍ ይናገራል።

‹‹ መከራው ጥቂት በጥቂት እያደባ ነው። ሰይጣን ጊዜው አጭር እንደሆነ ያያል።የምህረት ቀን እስኪፈጽምና የምህረት በር እስኪዘጋ ድረስ ሰዎች እንዲታለሉ እንዲስቱም እንዲያዝኑና እንዲያንቀላፉ እርሱ ወኪሎቹን ሁሉ በስራ ላይ አድርጎአቸዋል።DA636

“አውሎ ነፋስ (ማዕበል) በማይምር አኳኋን በመቆጣት እየወረደ ነው። ልንጋጠመው ዝግጁዎች ነን ወይ?”8T315

“አስፈሪ መፈተኛዎችና ፈተናዎች ያምላክን ሕዝብ የሚያቆያቸው ነው።”9T17

“ንግግር ሁሉ አስፈሪ የሆኑ ፍርዶች በአለም ላይ በቶሎ የሚወርዱ መሆናቸውን በመስማት ሊሰጥ አለበት።... እግዚአብሔር ሕዝቡን በዘለዓለማዊ ዳርቻዎች ላይ የሆኑ ወንዶችና ሴቶች ሆነው እንዲነቁ እና እንዲራመዱ ይረዳቸዋል።”8T37

ከግማሽ መቶ ክፍለ ዘመን በላይ ከሚሆነው ዘመን በፊት የጌታ አገልጋይ ጻፈች፡

“የክርስቶስ ወታደር ሁሉ ተግባሩ አድርጎ ቢሆን ኑሮ ዓለም ከዚህ በፊት የማስጠንቀቂያ መልዕክት በሰማ ነበር። ነገር ግን ስራው ብዙ አመታት ወደ ኋሊት ሆኗል።”9T29

“ለአለም የምህረትን መልዕክት በመስጠት ረገድ ያምላክ ሀሳብ በሕዝብ ተካሒዶ ቢሆን ኑሮ ክርስቶስ ከዚህ በፊት ወደዚህ ምድር በመጣ ነበር ጻድቃንም ወደ አምላክ ከተማ አቀባበል ባገኙ ነበር።” አንዳንዶች ‹‹አዎ ዳሩ ግን ብሄራዊው የእሁድ ሕግ ገና አልተላለፈም›› ለማለት ቢፈተኑም ተከታዩን ንግግር ደህና አድርገው ያስቡበት።6T450

“የኃይማኖት ንቃትና የቀደምትዋ ቤተ ክርስቲያን ኃይል እስቲ ይሁን የስደት መንፈስ ይነቃቃል የስደትም እሳቶች እንደገና ይነዳሉ(ይቀጣጠላሉ)”።GS48

የየሱስ መምጣት እንዲህ ለብዙ ዓመታት እንደ መዘግየቱ መጠን የእርሱ መምጫ ለማፋጠን እንዘጋጅ ዘንድ ስለዚሁ ብዙ ጊዜ የቆየበትን(የዘገየበተን) እርግጠኛውን ምክንያት በዚህ ጊዜ ተግተን በጸሎት ማጥናት አይገባንምን?

“ሰብአዊ ወኪሎች ከመለኮታዊ ወኪሎች (መንፈስ ቅዱስ፤ መላዕክት) ጋር ተባብረው ቢሰሩ ብዙዎች ነፍሳት ወደ እውነት ይመለሱ ነበር። ነገር ግን ያምላክ ነን የሚሉ ህዝብ በተመደበላቸው ስራ ላይ ሲያንቀላፉ ኖሯል።”9T46

እርሱ እወቁት“ መንፈስ ቅዱስ ለሚሰራባቸው መገናኛዎች በመጠባበቅ ላይ ነው።።...የእግዚአብሔር መንፈስ ዕቃዎች ይቀበሉት ዘንድ በቶሎ እንደ ተዘጋጁ ወዲያው በቤተ ክርስቲያን ላይ ይፈሳል።።”

ቅሬታዋ (ቤተ ክርስቲያን) በምድር ላይ ለሚመጣው እንዳልተዘጋጀች አየሁ።። ስንፍና እንደ ማንሳላጀት(ማንቀላፋት) ያለ የመጨረሻው መልዕክት እንዳለን እንደሚያምኑ በሚናገሩት በአብዛኞቹ አዕምሮዎች የተሰቀለ ይመስል ነበር።።... ለቅሬታዋ ትልቅ ስራ መስራት አለበት።።...መልአኩም አለ”ክፉ መልአኮች ጭፍራዎች በአካባቢያችሁ ናቸው።።”EW119,120

ሐሳቦቻችሁ ከዝግጅት ስራ በጣም በችኮላ የተጣመሙ እንዲሆኑ ትፈቅዳላችሁ(ትተውታላችሁ)።።... መልአኩም “ሰንበት ጠባቂዎች በራስ ዘንድ መሞት ይኖርባቸዋል አለ።።” ሆኖም ከምህረት ጊዜ መዘግያ(ማለቂያ) ላይና ለመከራ ጊዜ ከሚደረገው የዝግጅት ስራ ጋር ተያይዘው ያሉ ሁኔታዎች በግልፅ የቀረቡ ስለሆኑ እኛ ምንም ምክንያት የለንም።።”GC594

‹‹ያሁኑን እውነት እንደሚያምን የሚናገሩ ሁሉ ከጥቂቶቹ በቀር ለዚህ ጊዜ የሚሆነውን የዝግጅት ስራ በማስተዋል ረገድ ያልተዘጋጁ ናቸው።።››1T466

ክርስቶስ እውነተኛው ምስክር (ራዕይ1፡5) ብንቀበለው ለኋለኛው ዝናብ የሚያዘጋጀንን መልዕክት ለላውዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ልኮአል።።

<u>የላዶቅያ መልዕክት</u>

‹‹በሎዶቅያም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ። አሜን የሆነው÷ የታመነውና እውነተኛው ምስክር÷ በእግዚአብሔርም ፍጥረት መጀመሪያ የነበረው እንዲህ ይላል...

በራድ ወይም ትኩስ እንዳይደለህ ሥራህን አውቃለሁ። በራድ ወይም ትኩስ ብትሆንስ መልካም በሆነ ነበር።እንዲሁ ለብ ስላልህ በራድም ወይም ትኩስ ስላልሆንህ ከአፌ ልተፋህ ነው።ሀብታም ነኝና ባለጠጋ ሆኜአለሁ አንድም ስንኳ አያስፈልገኝም የምትል ስለ ሆንህ÷ ጐስቋላና ምስኪንም ድሀም ዕውርም የተራቆትህም መሆንህን ስለማታውቅ÷ባለ ጠጋ እንድትሆን በእሳት የነጠረውን ወርቅ÷ ተጐናጽፈህም የራቁትነትህ ኃፍረት እንዳይገለጥ ነጭ ልብስን÷ እንድታይም ዓይኖችህን የምትኳለውን ኩል ከእኔ ትገዛ ዘንድ እመክርሃለሁ።እኔ የምወዳቸውን ሁሉ እገሥጻቸዋለሁ እቀጣቸውማለሁ፤ እንግዲህ ቅና ንስሐም ግባ።እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ÷ ወደ እርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል።እኔ ደግሞ ድል እንደ ነሣሁ ከአባቴም ጋር በዙፋኑ ላይ እንደተቀመጥሁ÷ ድል ለነሣው ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ።›› ራዕይ 3፡14-21

ለላውዶቂያ የተላከው መልዕክት በምድር ታሪክ የመጨረሻው ቀናት ውስጥ ስላለችው የቅሬታዋ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ሁኔታ በእውነቱ የሚያመለክት ምስል ነው፡፡ የምህረት ጊዜ ከመዘጋቱ በፊት ክርስቶስ ለቅሬታዋ ቤተ ክርስቲያን የሚማጸነው የመጨረሻው ተማጽኖ ነው፡፡
‹‹ የላውዶቂያ ለብታምነትና የጎስቋላ ሁኔታዋ ምክንያቱ በልብዋ ውስጥ ራስ ነግሶ ለክርስቶስም ከበሩ ውጭ በመጣሉ ነው፡፡ የላውዶቂያ መልዕክት ‹‹የሚገርም ዘለፋ ነው፡፡›› ሆኖም የፍቅር መልዕክት ነው፡፡ ከታላቁ አፍቃሪ የፍቅር ተማጽኖ ነው፡፡ የእውነተኛ ምስክር ምክር ብንቀበልና ክርስቶስ በወኪሉ በመንፈስ ቅዱስ በውስጡ ሊገባ እንዲችል የልብን በር ብንከፍትለት የሚወረንን ኃጥያት ሁሉ ለማሸነፍና በዙፋኑ ላይ ከክርስቶስ ጋር የመቀመጥን ታላቁን መብት እንደሰትበት ዘንድ መለኮታዊ ኃይል እናገኛለን፡፡›› 3T252

ወርቅ . . . ፍቅርና እምነት(5T233)
ነጭ ልብስ. . . የክርስቶስ ጽድቅ ት. ዘካር 3፡5
የአይን ኩል. . . ኃጥያትንም ለይተህ የምትጠላበት፤(5T)

‹‹ ክርስቶስ በውስጣችን የሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ነው ያምላክ መንፈስ በኃይማኖት በልብ ውስጥ የተቀበለውን የዘለዓለም ህይወት መጀመርያ ነው፡፡›› ዘላለማዊው መዳረሻችን የሚያርፍበትን ስለዚሁ ዋና ጉዳይ ያምላክ መልዕክተኛ ከጻፈችው ጽሑፍ የተውጣጡትን ንግግሮች በጸሎት እናጥና፡፡DA388

“የእውነተኛ ምስክር ምክር ተስፋቢስ በሆነው ሁኔታ ለብ ባሉት አይመስልባባቸው፡፡ ሁኔታቸውን ለማቅናት አሁንም ቻንስ አላቸው የላውዶቂያ መልዕክት በማደፋፈሪያ የተሞላ ነው፡፡” RH August 28/1894

‹‹ለመጨረሻዋ ቤተ ክርስቲያን የተሰጠው ማስጠንቀቂያ ደግሞ ክርስቲያኖች እንደሆኑ ለሚናገሩት ሁሉ መታወጅ አለበት፡፡ የላውዶቂያ መልዕክት ሁለት ልሳን እንዳለው ስለታማ ሰይፍ ወደ አብያተ ክስቲያናት ሁሉ መሔድ አለበት፡፡ … ቤተ ክርስቲያናት እንዲመከሩ ጥረትን ሁሉ አድናደርጋለን?››6T77

“ለላውዶቂያ ሰዎች ከቀረበው የእውነተኛ ምስክር መልዕክት እነዚህ ምን ጠባይ ያበጁ ይሆን? እዚህ ላይ ምንም ማታለል ሊሆን አይችልም፡፡ ይህ መልዕክት በእግዚአብሔር አገልጋዮች ለብ ላለችው ቤተ ክርስቲያን መቅረብ አለበት፡፡ በአምላክ ፊት ባላቸው እርግጠኛ አቋማቸው እረገድ ከጸጥታነታቸውና ከአስጊ ማታላያቸው ህዝቡን መነቃቃት አለበት፡፡ ይህ ምስክር ከተቀበሉት ለተግባር ያነቃቃል ራስን ወደ ማዋረድና ዝቅ ወደማድረግ ኃጥያትንም ወደመናዘዝ ይመራል፡፡”3T259

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ለምንድ ነው? የሦስቱን መላዕክት መልዕክት ለማዳረስ ያልቻለችው? ለዚህ ጥያቄ መልስ በቀጣዮቹ ክፍል እንመለከታለን፡፡

የሰይጣን አሳችነት

‹‹ሰይጣን ከተቻለ በዚያ ቀን ይቆሙ ዘንድ ዝግጅድት እንዳያደርጉ ይከለክላቸዋል፡፡እርሱም መንግዳቸውን እንዲያጥርባቸው በምድራዊ መዝገቦችም ሊያደናቅፋቸው ከባድ የሆነ አሰልቻች ሸክም እንዲሸከሙ እያደረጋቸው እንዲሁም ጉዳዮችን ያሰናዳላቸዋል፤ ልቦቻቸው በዚህ ህይወት ጥንቃቄ ላይ እንዲያርፍ እና የመፈተኛው ቀን እንደ ሌባ ይመጣባቸው ዘንድ፡፡›› GC625,626

“የሠይጣን ኃይሎች ከዘላለማዊ እርግጠኝነት ሐሳቦችን እንዲያጣመሙ ለማድረግ በስራ ላይናቸው፡፡ ጠላት ለገዛ ሀሳቦቹ እንዲስማሙ ነገሮችን አደላድሉል፡፡ አለማዊ ስራ ስፖርት የቀኑ ቅምጥልናዎች እኒህ የወንዶችንም የሴቶችንም አዕምሮ ይይዛሉ፡፡”9T43

“ሐሳብን ከሚማርኩ ሺህ ጉዳዮች መራቅ አለብን፡፡ ጊዜን የሚያጠፋና መመራመርን የሚያነሳሱ ነገሮች አሉ፤ ዳሩ ግን በምናምን ነገር ላይ የሚፈጸሙ ናቸው፡፡ እጅግ ከፍ ያሉ ሐሳቦች ቁም ነገር ላልሆኑት ነገሮች ብዙ ጊዜ የሚሰጠውን ጥብቅ ጥንቃቄና ኃይል ይጠይቃሉ፡፡ ”8T316

“መንፈሳዊ ህይወትን የሚመግበውንና የሚያነቃቃውን ምግብ ለነፍሶቻችን ለመስጠት ኃላፊነት እንዳለብን መሰማት ያስፈልገናል፡፡”

ሰው የሰይጣንን ሀሳቦችንን ይከተል ዘንድ በተፈጥሮ የሚያዘነብል ነው፤ እርሱም ክርስቶስ ኃያሉ አሸናፊ በእርሱ ውስጥ ኑሮ ምኞቶቹን ካልመራና ኃይል ካልሰጠው እንዲህ አስፈሪ የሆነውን ጠላት በክንውን ሊቋቋመው አይችልም ። በእግዚአብሔር ህዝብ ላይ በሚያደርገው የመጨረሻው ውጊያው እርሱ መሆኑ እንዳያውቁ ሰይጣን ማታለያዎቹን እያዘጋጀ ነው፡፡(1ቆሮ 11፡14)፡፡1T341

“ይህ ትጉ ጠላት በየጊዜው በድንኳናችን ነው፡፡ “GC508

ሰይጣን እኛን ከሰማይ ለማስቀረት የሚያደርገውን ጥረት አይናችው፡ ለከፍቶ ብናይ እውነተኛ እረኛ መሸሸጊያችን እናደርገው ነበር። ነብይቷ እንዲህ ብላ የፍቅር ማስጠንቀቂያ ትለግሰናለች።

“ክፎች መላዕክት በየጊዜው በድንኳናችን ላይ ናቸው”።1T302

“ለሁሉም እላለሁ ተጠንቀቁ(ትጉ) ሰይጣን አባሎችን የራሱ ወገን አድርጎ ሊመልሳቸው እየሞከረ ... እንደብርሃን መልዕክ በክርስቲያኖች ሠራተኞችና በየቤተ ክርስቲያኑ በሚደረገው ስብሰባ (ጉባዔ) ሁሉ ውስጥ ይሔዳልና።”8T294

“አምላክ መንፈሱ ሊያፈስ እንዲችል የእግዚአብሔር ህዝብ እንቅፋትን (ክልከላን) ሁሉ በማስወገድ መንገዱን የማመንጠራቸውን ያህል አብዝቶ የሚያስፈራ ነገር የለም።”COR149

“ከሰብዓዊ ልብ እራስን መውደድና ከርኩሰት ጋር ዘውትር ጦርነት ማድረግ አለብት።. . . አምላክን የሚረሱ ለአንዲት ሰዓት ወይም ለአንድ አፍታ ቢሆን እንኳን በአስጊ ጎዳና ውስጥ ናቸው።”ST397
“ክርስቲያን በማይተጋበት ጊዜ ሁሉ ይህን ኃይለኛ ባለጋራ ድንገተኛ የሆነ ብርቱ አደጋ ይጥልበታል።”5T394
“የሰይጣን ፈተናዎች ኃይል እየጨመረ ስለሚሔድ የምንሮርባቸው ጊዜያት ለአምላክ ልጆች በሚያሰጋ የተሞሉ ናቸው።” counsels to church p322
“በመጨረሻ ቀናትም የሠይጣን ኃይል በብዙ ሲጨማመር ከተቻለው የተመረጡትን እንኳን ያታልላል(ማቴ 24፡24)።” Spiritual gift p277

“አቋማችን እንደምን ከፍ ያለ ቢሆንም ግድ የለም፤ ዘውትር መትጋት እና መጸለይ ያስፈልገናል። እለት እለት ለእግዚአብሔር መንፈስ መገዛት አለብን፤ አለበለዚያ በሰይጣን መገዛታችን ነው።. . . እነዚያ ለአምላክ በፍጹም የማይቀደሱ በክርስቶስ አገልግሎት ያሉ መሆናቸውን ገናም እራሳቸውን ሲደልሉ ሳለ የሰይጣን ስራ ያደርጉ ዘንድ የሚመሩ ይሆናሉ።” 5T102,103

“ሰይጣን ሀሳቡን ቆርጦ በአምላክ መንፈስ ግዛት ስር የማይሆነውን አዕምሮ ሁሉ ይገዛዋል።” TM79

የአምላክን ህዝብ ማነቃቃት

ይህ ኃላፊነት የተጣለው በመጋቢዎች ብቻ ሳይሆን በካህናት ጭምር ነው።።ካህናት በአዲስ ኪዳን ራዕ 1፡6 ሁላችን መሆናችን ይገልጻል።።

“በእሳት ውስጥ የተሞከረውን ወርቅ፤ ነጭ ልብስ ና የዓይን ኩልን ትሻ ዘንድ የእውነተኛ ምስክርን ምክርን ትቀበለዋለህን? ወርቁ እምነትን፤ ነጭ ልብስ የክርስቶስ ጽድቅ፤ የዓይን ኩል መንፈሳዊ ማስተዋልን የሰይጣን ተንኮሎችን አይተህ የምትርቃቸው፤ ኃጥያትንም ለይተህ የምትጠላበት፤ እውነትን አይተህ ልትታዘዘው የሚያስችልህ ነው።።”5T233

“የላውዶቂያ መልዕክት ያሁኑን እውነት እንደሚያምኑ ስለሚሉት አመላክ ህዝብ ያመለክታል።። አበዛኛው ክፍል ስም ብቻ፤ ነገር ግን መንፈሳዊ ቅናት የሌላቸው ለብ ያሉ ፕሮፌሰሮች ናቸው።።. . . በራስ ዘንድ መሞትን የማይፈቅዱ ናቸው።።”4T87

ቀዳሚዎቹ ጥቅሶች ያምላክን ሕዝብ የላውዶቂያ መልዕክት በመቀበል በኋለኛው ዝናብ ጊዜ የሦስቱን መልአክ መልዕክት በታላቅ ኃይል ያውጁ ዘንድ የሚዘጋጁ መሆናቸውን ይገልጻል። ሆኖም የላውዶቂያ ሰዎች መንፈሳዊ ድህነታቸውን የማይገነዘቡና የክርስቶስን የእውነተኛው ምስክር ምክርን ሊከቱሉ የማይፈቅዱ ይነቃቀላሉ።

“ስለየሁት መነቃነቅ ትርጋሜውን ጠየቅሁና ለላውዶቅያ ሰዎች በእውነተኛ ምስክር ምክር በሚቀርበው ትክክለኛው ምስክርነት የሚደረግ መሆኑን ታየኝ። ይህ በተቀባዩ ልብ ውስጥ ፍሬው ይኖረዋል፤ ሰንደቅ አላማውን ከፍ ለማድረግ ቀጥተኛውን እውነት ለማብሰር ይመራዋል። አንዳንዶች ይህን ቀጥተኛውን ምስክርነት አይዙም። በተቃዋሚነት ይነሱበታል፤ በአምላክ ህዝብ መኻከል መነቃነቅት የሚፈጥር ይህ ነው።።” EW270

የመጨረሻውን መልዕክት የሚቀበሉ በአስጨናቂው መከራ ወቅት አይነቃነቁም። ክርስቶስ ይህን በምሳሌ በነገረን ታሪክ ላይ ለቅሬታዋ ምን ላይ መመስረት እንደሚገባት ተናግሩል።

“ይህን ለቅሬታዋ የቀረበውን የመጨረሻውን መልዕክት ብንቀበል አንነቃነቅም። ብሔራዊ የእሁድ ህግ ሲጸና ታላቅ መፈተኛ ላይ መቆማችን ነው፤ የኋለኛውን ዝናብ እንለማመደዋለን። ከፍ ባለውም ጩኸት ጊዜ በታላቅ ኃይል መልዕክቱን በመስጠት እረገድ ተካፋዮች እንሆናለን። “

የኋለኛው ዝናብ አሁን የሚያስፈልገን ነው

“መላው ዓለማት በመልካም እና በክፉ መኸከል ስለሚሆነት የመጨረሻዎች ታላቁ ጋድሎ ሁሌታዎች ተገልጾ በማያልቅ አኪኋን ሐሳባቸውን ጥለውበት በመጠባበቅ ላይ ናቸው። የእግዚአብሔር ህዝብ ወደ ዘላለማዊ ዓለም ዳርቻዎች ላይ እየቀረቡ ናቸው።” PK148

ሮሜ9:28‹‹ጌታ ነገሩን ፈጽሞና ቆርጦ በምድር ላይ ያደርገዋልና ብሎ ስለ እስራኤል ይጮኻል።››

“መንፈስ ቅዱስ ለአገልግሎት ነው የሚሰጠን ለገዛ እራሳችን ምርጫ ስራ አይደለም ፤ ነገር ግን እንድናደርግ አምላክ ለሚጠራንበት ስራ ነው።እኛ መንፈስ ቅዱስ ልንጠቀምበት አንችልም። መንፈስ ቅዱስ ሊጠቀምብን ይገባል። በመንፈስ ቅዱስ አመካኝነት እግዚአብሔር ‹‹ እንደ መልካም ፈቃዱ እንዲፈቅዱና እንዲያደርጉ›› በህዝቡ ውስጥ ይሰራል።” DA672

የመንፈስ ቅዱስ ለዋጭ ኃይል

ዮሐንስ 3፤ 4 ያንብቡ።

“ያለ አምላክ መንፈስና ኃይል እውነትን ለማቅረብ የምንሰራው በከንቱ ይሆንብናል።።” 5T153

ኃጥያትን ሳንተው የእግ/ርን መድረክ ባንዳፊር መልካም ነው። ይህን ማድረጋችን ለእኛ ነው የሚጠቅመን። ያልኖርንበት አውርተን የተጣልን እንዳንሆን እንጠንቀቅ።

መንፈስ ቅዱስን በየቀኑ ልንሞላ ያስፈልጋል። ጌታ የጠራን ከስጋ ስራ ወደ መንፈስ ፍሬ መሆኑን መዘንጋት የለብንም። እነዚህን የመንፈስ ፍሬዎች በህይወታችን ልንለማመዳቸው ያስፈልገናል።

“ክርስቶስ ታላቁ መምህር የሚመርጥባቸው ወሰን የሌላቸው ልዩ ልዩ አርስቶች ነበሩት ዳሩ ግን አብዛኛውን እርሱ የኖረበት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ነበር። ስለዚህ ስጦታ ስለ ቤተ ክርስቲያኒቷ ምንኛ ታላላቅ ነገሮች የተተነበየ ነው። ሆኖም ግን አሁን በአነስተኛው የኖሩበት ምን አርስት ነው?።”1SM156

“ሰውን ወደ አምላክ አምሳልነት እንዲመልሰውና ያምላክን ስራ እንዲያደርግ ያስችለው ዘንድ ከራሱ ውጭ ወዲያ አልፎ ኃይል ያስፈልገዋል፤ . . . ሰብዓዊነት መለኮታዊ ኃይልን ይጨብጣል፤ ክርስቶስም በኃይማኖት በልብ ውስጥ ይኖራል፤ ከአምላክ ጋር በትብብር መስራቱ የሰው ኃይል ለመልካም ነገር ብቁ ይሆናል።”DA296,297

“ብዙዎች የፊተኛውን ዝናብ ለመቀበል በብዙ አዳግቶቸዋል። እግዚአብሔር እንዲሁ ያሰናዳላቸውን ጥቅሞች ሁሉ አላገኙም። እነርሱም የተጓደለው ጉድለት በኋለኛው ዝናብ የሚሞላ መሆኑ ተስፋ ያደርጋሉ። እጅግ የበለጸገው የጸጋ ብዛት ሲሰጥ ለቀበሉት ልቦችን ለመክፈት ያስባሉ። እነርሱ አስፈሪ ስህተት ማድረጋቸው ነው።. . . ባንሻሻል የፊተኛውና የኋለኛውን ዝናብ በምንቀበልበት አስታያየት ላይ እራሳችን ባናኖር ነፍሶቻችንን እናጣለን ኃላፊነትም በበራች ላይ ይኖራል።”TM507,508

“መንፈስ ቅዱስ በልባችን ውስጥ በሚሰራው ስራ አማካኝነት ብቻ ለሰማይ ተገቢሆች ለመሆን እንችላለን፤ ወደ አብ አቀራረብን ለማግኘት ብንፈልግ፤ ለዋስትናችን የክርስቶስ ጽድቅ ሊኖረን ይገባል

የክርስቶስ ጽድቅ ይኖረን ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ ተጽዕኖ ዕለት ዕልት መለወጥ፤ መለኮዊ ብህሪዎች ተካፋይ መሆን ያስፈልገናል። ጠባይን ከፍ ማድረግ፤ ልብን መቀደስ፤ መላውን ሰው ማሳመር የመንፈስ ቅዱስ ስራ ነው።።" 1SM374

አስፈላጊው የፊተኛው ዝናብ

ገላ 5፡21 የሚገኙት የመንፈስ ፍሬዎች በህይወታችን ስለመኖራቸው ራሳችንን እንጠይቅ።።

"ከራስህ ትወገድ ዘንድ ዛሬ ራስህን ለአምላክ መሰጠት አለብህ ።።. . . ለኋለኛው ዝናብ ጎርፎች ዝግጁ እንዲሆን ዕቃህን ዛሬ አንዲነጻ ማድረግ አለብህ፤ . . . የኋለኛው ዝናብ ይመጣልና ያምላክ በረከት ከርኩሰት የሚነጻውን ለሚያለመልመውም ጊዜ የተገባውን፤. . . ለመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የተገባውን ነፍስ ሁሉ ይሞላበታልና።።"1SM191

"በማንኛውም ነገር ሁሉ የሚዘልቁ እና ፈተናን ሁሉ የሚቋቋሙና የሚያሸንፍ ዋጋው፤ የሆነ ቢሆን የእውነተኛውን ምስክርነት ምክር የተቀበሉ እነርሱም የኋለኛውን ዝናብ ይቀበላሉ፤ እንዲሁ ለመውሰድ የተገቡ ይሆናሉ።።"1T187,188

"መንፈስ ቅዱስ የሌላቸው በጺዮን ግንቦች ላይ የታመኑ ጠባቆች ሊሆኑ አይችሉም፤ ሊደረግ ለሚገባው ስራ እውሮች ናቸውና ለመለከትም የተለየ ድምጽ የሚሰጡለት አይደሉምና።።"2SM57

"መንፈስ ቅዱስ ሲፈስስ የፊተኛውን ዝናብ ያልተቀበሉና ያልወደዱት የኋለኛው ዝናብ ዋጋነት የማያዩ ወይም የማያስተውሉ መሆናቸውን እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን።።" TM399

አሁን ለኋለኛው ዝናብ መዘጋጀት

የጠባያችንን ልብሶች ማጠብና በበጉ ደም ነጭ ልናደርጋቸው የሚገባን አሁን ነው። ትዕቢትን፤ፍትወትንና ስንፍናን ማሸነፍ ያለብን አሁን ነው።።ጠባይን ለማነጽ መንቃትና ቁርጠኛ ጥረት ማድረግ ያለብን አሁን ነው።።‹‹ዛሬም ድምጹን ብትሰሙ ልባችሁን አታደንድኑ››። እኛ ያለን እጅግ ፈታኝ በሆነው ሁኔታ ውስጥ ነው፤ የጌታችንም መገለጽ በመቆየት እና በመጠባበቅ ላይ ነን። አለም በጨለማ ውስጥ ነው ።።‹‹እላንት ግን ወንድሞቼ ይላል ጳውሎስ በጨለማ አይደላችሁም . . . ›› በታላቁ የዝግጅት ስራ ምን እያደረግን ነው፤ ወንድሞቼ? ከአለም ጋር የሚተባበሩቱ ዓለማዊ ቅርጽ ተቀብለው ለአውሬው ምልክት የሚዘጋጁ ናቸው። እነዚህ በራስ የማይታመኑ በአምላክ ፊት ራሳቸውን ትሁት የሚደርጉትና እውነትን በመታዘዝ ነፍሶቻቸውን የሚያንጹ እነዚህ ሰማያዊ ቅርጽን ይቀበላሉ፤ በግንባሮቻቸው ላይ ለአምላክ ማህተብ የሚዘጋጁ ናቸው። አዋጁ ሲወጣና ማጎተምም ሲታተም ጸባያቸው ለዘላለም ንጹህና ነውር የሌለበት ሆኖ ይቀራል።።8T216

“የባህሪያችን ወራት ሀሳብ አይደለም የአዕምሮም ችሎታ ወይም የልብ ዝንባሌ አይደለም፤ የሚፈለገው ዳሩ ግን በየጊዜው በአምላክ መንፈስ አገታት ስር መሆን የሚያሻው ነው። ”PP421

የኋለኛው ዝናብ ፤ የክርስቶስ ልብ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በየቀኑ መቀበል

“በላንተ በክርስቶስ የሱስ የነበረ ልብ ይሁንባችሁ።።”ፊሊ 2፡5

“እንከተለው ዘንድ የተሰጠን ክርስቶስ አርያችን ፍጹምና ቅዱስ ምሳሌያችን ናቸው።።”KH265
“ክርስቲያን መሆን የክርስቶስን ስም መቀበል ብቻ አይደለም፤ የክርስቶስ ልብ ማግኘት በሁሉ ነገሮች ለአምላክ ፈቃድ መገዛትም ነው።።”KH174
“ክርስቶስ ለእኛ ይናገር ዘንድ ዘውትር(መንፈስ ቅዱስ) ይቀበል ነበር።። . . ለራሱ ሳይሆን ለሌሎች እርሱ ኖረ፤ አሰበ ጸለየም...

ከአምላክ ጋር ባሳለፍነው ሰዓታት የሰማይን ብርሃን ለሰዎች ያመጣ ዘንድ በየጠዋቱ ይወጣ ነበር። በየቀኑ የመንፈስ ቅዱስ አዲስ ጥምቀት ተቀበለ።”COL139

“መንፈስ ቅዱስ ለሰው ዘወትር መሰጠት አለበት አለበለዚያ የጨለማ ኃይሎች ለመቋቋም አቅም የለውም።”KH16

የአምላክ ፍቅር
ሮሜ 5፡5 ‹‹የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ፈሳለችና በመንፈስ ቅዱስ ለእኛ የተሰጠ››
‹‹የመንፈስ ቅዱስ በውስጣችን መኖር የሚታየው የሰማያዊው ፍቅር በመፍለቁ ነው።››COL419

በሰው አማካኝነት የመድኃኒታችን ፍቅር የመገለጹ ያህል አለም የሚያስፈልገው ነገር የለም።COL419

“የክርስቶስ ፍቅር፤ የወንድሞች ፍቅር ከእየሱስ ጋር እንደ ነበርንና ስለ እርሱሰ እንደተማርን ለአለም ይመሰክራል። በዚያን ጊዜ የሦስቱን መልአክ መልዕክት ከፍ ባለ ጩኸት ያስተጋባል፤ መላው ምድር በጌታ ክብር ይበራል።”6T401

“ለእለታዊ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሠራተኛ ሁሉ ልመናውን ለአምላክ ማቅረብ አለበት።”AA

<u>ሄኖክና ዮሐንስ መጥመቂ አምላክን ማወቅ</u>

“ከአሁን በፊት ከቶ ያልታየ ግስጋሴ አለምን እያጥለቀለቀ ነው። በመደሰቻ ጩዋታ ገንዘብን በማጠራቀም ለኃይልም ተጋድሎ በማድረግ ለኑሮም በመታገል፤ አካልን ሃሳብን ነፍስንም የሚማርክ አስፈሪ ኃይል አለ።በዚህ የእበደት መራራጥ መሀል አምላክ እየተናገረ ነው።”ED260

Er 9:23

ገፅ 26

“አምላክንና የሱስን ማወቅ፤. . . የሰማይ ከተማደጆችን የሚከፍት ቁልፍ ነው”MH457

“እግዚአብሔርና የላከውን የሱስ ክርስቶስን በልምምድ ማወቅ ሰውን ወደ አምላክ አምሳል ይለውጣል።”COL114

የጠባይ መለወጥ የሚሰራ አምላክንም ማወቅ በብዙ የሚያስፈልገን ነው። ሃሳቡን ብንፈጽፍም ከቃሉ ጋር የሚስማማ ያምላክ ገለጻ በሂወታችን ውስጥ መሆን አለበት። “የሄኖክና የመጥመቁ ዮሐንስ ልምምድ እኛ ምን መሆን እንደሚገባን የሚያመለክት ነው። ከምናደርገው የበለጠ የነዚህ ሰዎች ሕይወት ማጥናት ያስፈልገናል ይህውም ሞት ሳያይ ወደ ሰማይ የተወሰደውንና ከክርስቶስ መጀመርያ መምጫው በፊት የጌታን መንገድ ለማዘጋጀት ጎዳናዎችንም ለማስተካከል የተጠራውን። ”8T329

ሄኖክ

‹‹ሄኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ አልተገኘም እግዚአብሔር ወስዶታልና።››ዘፍ 5፡24

‹‹. . . ሳይወሰድ እግዚአብሔርን ደስ እንዳሰኘ ተመስክሮለታልና፤››ዕብ 11፡5

“የሄኖክ ከአምላክ ጋር መሄድ በቅዠት ወይም በራዕይ አይደለም፤ ዳሩ ግን በእለታዊ ህይወቱ ተግባሮቹ ሁሉ እንጂ። እርሱ ስራሱ ፈጽሞ ከአለም ዘግቶ ባህታዊ አልሆነም በአለም ለአምላክ የሚያደርገው ስራ ነበራውና።”PP85

“. . . የሄኖክ ልብ በዘላለማዊ መዝገቦች ላይ ነበር። በምድር ገና ሳለ እርሱ በታይማኖት በብርሃን ግዛት ውስጥ ኖረ።”8T330

“ልቡ ከአምላክ ፈቃድ ጋር ስሙሙ ነበር።. . . ሄኖክ ብርቱ የሆነ በጣም ያማረ ሐሳብና ሰፋ ያለ እውቀት የነበረው ሰው ነበር፤ ከአምላክም ባገኘው ልዩ ራዕዮች የተከበረ ነበረ ነበር፤ ይሁን እንጂ መለኮታዊ ታላቅነቱ ፍጹም ዘወትር በፊቱ መሆን በተሰማው ሀሳብ ከሰማይ ጋር ዘወትር ግኑኝነት በማድረጉ እርሱ እጅግ ትሁታን ከሆኑ ሰዎች አንዱ ነበር.....

ገፅ 27

ከአምላክ ጋር የተቀራረበ ግኑኝነት እንደማድረጉ መጠን፤ ስለ ራሱ ደካመነትና ፍጹምነት የሌለው መሆኑ የተሰማው ሀሳብ የጠለቀ ነበር።”PP85

“ዛሬ ትልቁ ፍላጎታችን በአምላክ መንፈስ ቅዱስ የሚጠመቁትን ሂኖክ እንደሂደ ከአምላክ ጋር የሚሂዱ ናቸው።”ST

“ሂኖክ እንዳደረገ በአምላክ ፊት የሚሂድ ህዝብ የሚያስፈልገን ከሆነ ሰባተኛው ቀን አድቬንቲስቶች አሁን እንዲሁ ማድረግ ያስፈልጋቸዋል።”7T155

መጥመቁ ዮሐንስ

“እግዚአብሔር የዘካርያስን ልጅ ለታላቅ ስራ ጠርቶት ነበር።”DA100

“እንዲህ ያለ መልዕክተኛ ቅዱስ መሆን አለበት። በውስጡ ለሚኖረው የአምላክ መንፈስ መቅደስ መሆን አለበት።”DA100

“ዮሐንስ እንደሠጠ እንዲህ ያለ መልዕክት ለመስጠት እንደርሱ መንፈሳዊ ልምምድ ሊኖረን ይገባል። አምላክን መመልከት አለብን እርሱን በመመልከት ራስን አለማየት ነው።8T333

“ዩሐንስ መጥመቁ በበረሃ ህይወቱ ስለ እግዚአብሄር ተማረ።በተፈጥሮ የአምላክን ገለጻዎች አጠና በመለኮታዊ መንፈስ መሪነት የነቢያት ብራናዎች አጠና። በሌትና በቀን ክርስቶስ ጥናቱ ሃሳቡ ነበር ። አዕምሮውና ልቡን ነፍሱንም በከበረው ራዕይ እስኪሞሉ ድረስ።”8T331,332

የኋለኛው ዝናብ

የፊተኛው ዝናብ በየቀኑ የአማኙን ልብ እየሞላ የሚለውጥ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው።ይኸውም በኃጥያት ላይ ድል የሚሰጥና በክርስቶስ ጽድቅ የሚሸፍን ነው። የኋለኛው ዝናብ ለመመስከር ኃይል ነው። የሦስተኛው መልአክ መልዕክት ከፍ ያለውን ጩኸት በአስገዳጅ ኃይል ለመስጠት የአምላክ የታመነችው ቅሬታ ያዘጋጃል። በዚያን ጊዜ የአለም ዓይን በአምላክ ትዕዛዝ ጠባቂ ሕዝብ ላይ ያተኩራል።

“የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ የሚሆንበት ጊዜ፤ ይኸውም ኃያሉ መልአክ ሲውርድ ለዚህ ዓለም የሚሆነውን ስራ በመዝጋት ረገድ ከሦስተኛው መልአክ ጋር የሚተባበርበትን ጊዜ ለመናገር የተለየ ጊዜ የለኝም፤ መልዕክቴን መብራቶቻችንን አሰማምረንና አቀጣጥለን ለሰማያዊው እረፍት ዘመን በመዘጋጀት ብቻ ደህንነት እናገኛለን።”1SM192

የአምላክ አገልጋይ ስለ መንፈስ መፍሰስ የተለየ ጊዜ ባታመለክተንም፤“በትንሹ የመከራ ጊዜ ጅምር ላይ ፤. . . የኋለኛውን ዝናብ ውይም አለምላሚውን ከአምላክ ፊት እንደሚመጣ›› ትናገራለች”። ይህም መቅሰፍት ከመውረዳቸው በፊት አጠር ያለ የመከራ ጊዜ ነው። የሰው ዘር በሁለት ክፍሎች የሚከፈልበት የአውሬውን ምልክት የሚይዙና በግባሮቻቸው የአምላክ ስም ወደሚይዙበት ወደዚያ ጊዜ በመቅረብ ላይ ነን።EW85,86

“የአምላክ ፍርዶች በምድር ላይ የመጨረሻ ጉብኝቱን ከመሰንዘሩ በፊት፤ ከሐዋርያት ጊዜያት ወዲህ ታይቶ የማይታቀቅ የጥንቱ አምላካዊ አምልኮ የመሰለ መነቃቃት በጌታ ህዝብ ይሆናል። የአምላክ መንፈስ ኃይል በልጆቹ ላይ ይፈሳል።”GC464

“በመከራ ጊዜ ጅምር ላይ ወጥተን ስለ ሰንበት በይበልጥ አሟልተን ስለተናገርን በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተን ነበር።”EW85

የመከራ ጊዜ ተብሎ የተጠቀሰው በትንሹ የመከራ ወቅት ላይ ነው።

“. . . የስደት አውሎነፋስ በርግጥ በእኛ ላይ ሲፈነዳ እውነተኞቹ በጎች የእውነተኛ እረኛን ድምጽ ይሰማሉ። እራስን የመካድ ጥረቶች የጠፉትን ለማዳን ይደረጋሉ። ከመንጋውም ተቅበዝብዘው የነበሩት ብዙዎች ታላቁን እረኛ ይከተሉ ዘንድ ይመለሳሉ።”. . . 6T401

“ትልቁ ብርሃን ሲያርፍባቸው አየሁ እነርሱም የሶስተኛውን መልአክ መልዕክት ያለ ፍርሃት ይናገሩ ዘንድ ተባበሩ።”EW227-229

“የአምላክ አገልጋዮች ከላይ ኃይል ተጎናጽፈው ፊቶቻቸው በርተው በተቀደሰው ቅድስና እያበሩ ከሰማይ መልዕክትን ይናገሩ ዘንድ ወጡ። በኃይማኖታዊ አካሎች ሁሉ ተበታት ነው የነበሩት ነፍሳት ለጥሪው መለሱ፤ ሎጥ ከመጥፋትዋ በፊት ከሰዶም ፈጥኖ እንደወጣ ከተፈረደባቸው አብያተ ክርስቲያናት የነበሩት ፈጥነው ወጡ።”GC612

“የሶስተኛው መልአክ መልዕክት ወደሚዘጋበት ጊዜ አስመለከተኝ። የአምላክ ኃይል በህዝቦቹ ላይ አርፎ ነበር፤ እነርሱም ስራቸውን ፈጽመው ነበር፤ ከፊታቸውም ላለው ፈታኝ ሰዓት ተዘጋጅተው ነበር። የኋለኛው ዝናብ ወይም ከአምላክ ፊት የሚያለመልመውን ተቀብለው፤ ሕያውም ምስክር ተነቃቅቶባቸዋል። የመጨረሻ ታላቁ ማስጠንቀቂያ በየስፍራው አስተጋብ□ል መልዕክቱንም ሊቀበሉ ያልፈለጉትንም የምድር ነዋሪዎች አነሳስቶአቸውና አስቆጥቱቸው ነበር።”EW279

“ጌታ ነግሩን ፈጽሞና ቆርጦ በምድር ላይ ያደርገዋልና ብሎ ስለ እስራኤል ይጮኻል።”ሮሜ 9:28


ኢሳ 8:1 ያለው ትንቢት ድጋሚ ይፈጸማል።

የምህረት ጊዜ መፈጸም

“መልአክ በሰማይ ወዲህና ወዲያ ሲሯሯጡ አየሁ። አንድ መልአክ የጸሐፊው የቀለም ቀንድ በጉኑ ይዞ ከምድር ተመለሰና ስራውን እንደሰራና ጻድቃንም እንደተቆጠሩ፤ እንደታተሙ ለእየሱስ ነገረ..

ከዚያም በኃላ አስርቱ ትዕዛዛት በያዘው ታቦት ፊት ሲያገለግል የነበረውን የሱስን፤ ማዕጠኑን ወዳታች ሲወረውር አየሁ። እርሱም እጁን አንስቶ በታላቅ ድምጽ ‹‹ተፈጸመ›› ሲል ተናገረ። መልአክ ሰራዊነት ሁሉ ጥብቅ የሆነ ንግግር ፤‹‹ግፍ የሚሰራ ግፍ ይስራ ደግሞ ከዕርኩስ የሚሆን እርኩስ ይሁን ደግሞ፤ ጻድቁ ይጽደቅ ደግሞም ቅዱሱ ይቀደስ ደግሞ፤ ›› ሲል በተናገረ ጊዜ አክሊሎቻቸውን አነሱ።” EW279- 281

ጌታ ይባርካችሁ



በትምህርቱ ብዙ እንደተባረካችሁ አምናለሁ በትምህርቱ በኩል አስተያየትና ጥያቄ ያላቸው በስልክ ቁጥር 0988737827 (ጌታያውቃል) በመደወል መስጠት ትችላላችሁ እንዲሁም በSpecial Prophecy Study (SPS) Telegram Group በመቀላቀል የበለጠ የበረከቱ ተካፋይ እንድትሆኑ በጌታ ፍቅር እጠይቃለሁ